# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምገባ ኤጀንሲ

## የግብዓት ማፈላለግ፣ማሰባሰብና ማስተዳደር የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 113/2014

2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

የተማሪዎችንና የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የግብዓት ማፈላለግን፣ ማሰባሰቡንና ማስተዳደሩን የሚመራበት ህጋዊ ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

ከተለያዩ አካላት በስጦታና በድጋፍ ወደ ኤጀንሲው የሚገባ ግብዓት ከብክነት በፀዳ፣ ግልጽና ወጥ የሆነ የመንግስት የንብረት አስተዳደር አሰራር ሥርዓትን ለመዘርጋት፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምገባ ኤጀንሲ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 74/2014 አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ (2) ተራ ፊደል (ሠ) መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምገባ ኤጀንሲ የግብዓት ማፈላለግ፣ ማሰባሰብና ማስተዳደር የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 113/2014 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1. "??? " ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤
2. "??????" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
3. "**ግብዓት**" ማለት ምገባ ኤጀንሲ ለማጠናከር የሚሰበሰብ ገንዘብና ንብረት ነው፤
4. "**የግብዓት አስተዳደር**" ማለት የምገባ ኤጀንሲ ለማጠናከር የተሰበሰበውን ሀብት በአግባቡ የመያዝ፣ የማስቀመጥ፣ ከልዩ ልዩ ብልሽትና ብክነት የመጠበቅ እንዲሁም ከተሰበሰበው ሀብት መካከል የተወሰነውን በማስቀረት በቦርዱ ውሳኔ መሰረት

ለተለያዩ ተጠቃሚ አካላት በድጋፍ መልክ የመስጠት፣ የማስተላለፍ፣ የመከታተልና የመቆጣጠር ተግባራትን ያጠቃልላል፤

5. "ድጋፍ" ማለት ምገባ ኤጀንሲን ለማጠናከርና የሚሰጠውን አገልግሎት ተጠቃሚ ለሆኑ አካላት የሚደረግ የምግብና ቁሳቁስ ድጋፍ ነው፤
6. "ስጦታ" ማለት የምገባ ኤጀንሲን ለማጠናከርና ተጠቃሚዎች ለመደገፍና ለማቋቋም የሚሰጡ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች ልገሳን ያጠቃልላል፤
7. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይንም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

4. <u>የፆታ አገላለጽ</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው አገላለጽ የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>የመመሪያው ዓላማና መርሆች</u>

5. <u>የመመሪያው ዓላማ</u>

የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለመደገፍ እንደ የችግሮቻቸው አግባብ ግብዓት በማፈላለግ፣ በማሰባሰብ፣ በማስተዳደርና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ለጠቃሚዎች ተደራሽ በማድረግ በዘላቂነት ያለው ግብዓት አቅርቦት የረኩ ዜጎች መፈጠር ነው፡፡

6. <u>የሀብት አሰባሰብና አስተዳደር መርሆዎች</u>

የሀብት አሰባሰብና አስተዳደር ሥርዓት በሚከተሉት መርሆዎች የሚመራ ይሆናል፡-

1. መላውን ህብረተሰብና ባለድርሻ አካላትን በብቃት በማሳተፍና ንቅናቄ በመፍጠር በፈንዱ የሀብት አሰባሰብ ሂደት የላቀ ሚና እንዲጫወቱ ማስቻል፣
2. ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው የሀብት አሰባበሰብ፣ አስተዳደርና ስርጭት እንዲኖር የሚያስችል ስርዓት መዘርጋትና መተግበር፣

3. ከባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ትብብር፣ ትስስርና ቅንጅታዊ አሰራር መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ፣
4. የተሰበሰበውን ሀብት በአግባቡ ማስተዳደርና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ፣
5. የሀብት አሰባሰብ፣ አስተዳደር፣ ስርጭትና ድጋፍ አሰጣጥና አሰራር በዘመናዊ የመረጃ ስርዓት የተደገፈ በማድረግ ተዓማኒነት እንዲኖረው ማስቻል፣
6. የሀብት አሰባሰብ፣አስተዳደር፣ ስርጭትና ድጋፍ አሰጣጥ አግባብ በግልጽ መረጃ ላይ የተመሰረተ የማድረግ አሰራር መከተል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>የምገባ ኤጀንሲ የግብዓት ወይም ቁሳቁስ አሰባሰብ ምንጮች፣ አይነቶችና ስልቶች</u>

### 7. <u>የምገባ ኤጀንሲ የግብዓትና ቁሳቁስ ምንጮች</u>

የምገባ ኤጀንሲ የሀብት ምንጮች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

1. የከተማ አስተዳደሩ የሚመድበው በጀት፣
2. ከከተማው አስተዳደር የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ፣
3. ከህብረተሰቡ የሚሰበሰብ ድጋፍና ስጦታ፣
4. ከንግዱ ማህበረሰብና ከተለያዩ ግለሰቦች የሚሰጥ ልዩ ልዩ ድጋፍ፣
5. ከሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች የሚገኝ እርዳታና ድጋፍ፣
6. ከሐይማኖት ተቋማት የሚገኝ ድጋፍና ስጦታ፣
7. ከመንግስት ልማት ድርጅቶች የሚሰጥ ድጋፍና ስጦታ፣
8. ከእድር ወይም ከሚዲያ ተቋም የሚሰጥ ድጋፍና ስጦታ፣
9. ከሲቪክ ማህበራት የሚደረግ ድጋፍና ስጦታ፣
10. ከሌሎች ህጋዊ ምንጮች፡፡

## 8. <u>ስለግብዓት ማፈላለጊያ ስልቶች</u>

ለምገባ ኤጀንሲ ሀብት ለማፈላለግ የሚከተሉት ስልቶች ስራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡-

1. ከማህበራዊ ትረስት ፈንድ ጋር በቅንጅት ይሰራል፣
2. ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ የድጋፍ ጥያቄ ማቅረብ፣
3. ለድጋፍ አድራጊ አካላት  ቀጥታ የድጋፍና የስጦታ ጥያቄ ማቅረብ፣
4. መንግስት ለዓላማው ድጎማና ድጋፍ እንዲያደርግ መጠየቅ ፣
5. የድጋፍና የሀብት ማሰባሰብያ ፕሮግራሞችን፣የማስታወቂያና የፕሮሞሽን ስራ መድረኮችን ማዘጋጀት፣
6. በተለያየ መልኩ ድጋፍ ለማድረግ በራስ ተነሳሽነት ከሚመጡ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ተቋማት ድጋፍ መቀበል፣
7. ባለድርሻ አካላት የተለያየ የሃብት ማግኛ ስልቶችን ዘርግተው ማህበራዊ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያገኙትን የገንዘብ ድጋፍ በኤጀንሲው በኩል ወደ ማህበራዊ ትረስት ፈንድ ቋቱ እንዲያስገቡ ይደርጋል፤
8. ድርጅቶች ማህበራዊ ሃላፊነትን መወጣት የሚያስችሉ ህግጋቶችን መመሪያዎችን እንዲያወጡ ድጋፍ ማድረግ፣
9. ባለድርሻ አከላት በሚተገብሩት  የተለያየ የሃብት ማሰባሰቢያ ስራዎች የነቃ ተሳትፎ እነዲያደርግ ማድረግ ፡፡

## 9. <u>ስለሚሰበሰብ ግብዓት ወይም ቁሳቁስ ዓይነቶች</u>

ለምገባ ኤጀንሲ ማጠናከሪያ የሚሰበሰበው ሀብት ዓይነት የሚከተለው ይሆናል፡-

1. በገንዘብ የሚደረግ ድጋፍ፣
2. በዓይነት የሚደረግ ድጋፍና ስጦታ፣
3. በጉልበት የሚደረግ አስተዋጽኦ፣
4. በዕውቀት የሚደረግ አስተዋጽኦ፣
5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2)፤(3) ወይም (4) መሰረት በዓይነት፣ጉልበት ወይም በዕውቀት የሚደረገው አስተዋጽኦ ወደ ገንዘብ ተለውጦ ይመዘገባል፡፡

## 10. ስለ ግብዓት አሰባሰብ

1. ኤጀንሲው በራሱ ተነሳሽነት በሚያቀርበው ጥያቄ ወይም በሌሎች ህጋዊ ምንጮች በጎ ፍቃድ ግብዓት ወይም ቁሳቁስ ያሰባስባል፤

2. ለህብረተሰቡ፣ ለባለድርሻ፣ ለተባባሪ አካላት እና መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ አካላት በተለያዩ የመገኛኛ ብዙሃን እና መድረኮችን በመጠቀም ግንዛቤ መፍጠር፣ በማሳተፍና ማንቀሳቀስ፣

3. ልዩ ልዩ የሀብት ማሰባሰቢያ ዕቅዶችንና እና ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀት ለኤጀንሲው ኃላፊዎች በማቅረብና እንዲጸድቅ በማድረግ፣

4. በተዘጋጀው ዕቅድና ፕሮጀክት ላይ ድጋፍ ከሚያደርጉ አካላት ጋር ተቀራርቦ በመነጋገር፣ የድጋፍና የስጦታ መስጫ ሰነድ እና የስምምነት ሰነድ በማዘጋጀት፣

5. አስፈፃሚ መንግስታዊ ባለድርሻ አካላት በራሳቸው ተነሳሽነት ለራሳቸው ኣላማ ማስፈፀሚያ ወይም ለምገባ ኤጀንሲ የትኩረት አቅጣጫ ማሳኪያ የተለያየ የሀብት ማሰባሰቢያ ስራዎችን በመተግበር ገንዘብ ወደ ቋቱ እንዲገባ በማስደረግ፣

6. ከማህበራዊ ትረስት ፈንድ ጋር በመሆን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የድጋፍና ስጦታ መስጫ ወይንም የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም፣

7. በተፈረመው የድጋፍና ስጦታ ማቅረቢያ እና የስምምነት ሰነድ መሠረት የገንዘብ ድጋፍ እንዲደረግ የማህበራዊ ትረስት ፈንዱን የሂሳብ አካውንት በመስጠት፣

8. ቃል የተገባውን ሀብት ክትትል በማድረግ በማሰባሰብና ገቢ መሆኑን በማረጋገጥ፣

9. የተሰበሰበውን ሀብት ለማህበራዊ ትረስት ፈንድ ጽህፈት ቤት ንብረት ክፍል በሞደል ገቢ መሆኑን በማረጋገጥ፣

10. ከመንግስት ለሚደረገው ድጋፍ ወይንም ድጎማ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር የድጋፍ እና ድጎማ ፕሮፖዛል በማቅረብ፤ ሲፈቀድም ድጋፉ ወይም ድጎማው ወደ ማህበራዊ ትረስት ፈንድ አካውንት ገቢ መሆኑን በመከታተል፣

11. ገቢ ለተደረገ ሀብት ገቢ ላደረገው አካል ህጋዊ የገቢ ደረሰኝ መስጠቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

11. <u>ስለድጋፍ ተጠቃሚ አካላትና የድጋፉ አይነት</u>

1. የመንግስት ትምህርት ቤት ለሆኑ ተማሪዎች ሲሆን የሚደረገው ድጋፍም የምገባ ፕሮግራም፣የምገባ አዳራሽና ቁሳቁስ አቅርቦት፣ የተማሪ ደንብ ልብስ አልባሳት፣ የትምህርት ቁሳቁስ፣ ጫማና የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ ድጋፍ የሚደረግላቸው ይሆናል፡፡
2. ለማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ ለሆኑ ዜጎች የምገባ አገልግሎት ድጋፍ የሚደረግላቸው ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የግብዓት ወይም ቁሳቁስ አስተዳደር</u>

12. <u>ግብዓት ወይም ቁሳቁስ ስለማስተዳደር</u>

1. ማንኛዉም በጎ አድራጎት ድርጅት፣ ግለሰብ፣ የመንግሰት ተቋም ወዘተ ለኤጀንሲው በስጦታም ወይም በሌላ መንገድ ሊያደርግ ያቀደዉን ማንኛውንም ድጋፍ ከማድረጉ በፊት በግልፅ ደብዳቤ ለኤጀንሲው ማሳወቅ ይኖርበታል፤

2. የምግብ ግብዓት እና ሌሎች ተመሳሳይ አቅርቦቶች በድጋፍ፣ በስጦታና በአይነት በሚለገሱበት ጊዜ ኤጀንሲው በማኔጅመንት በማየት በወጥ አሰራር ይወስናል፤

3. የመንግሰትም ሆነ የግል ተቋም፣ ማንኛዉም በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ግለሰብ፣ ለኤጀንሲው የሚያመጡትን ድጋፍ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትረስት ፈንድ በሚፈቅደው መሰረት ኤጀንሲው በሚያዘጋጀው መጋዘን ውስጥ ለአደጋ እና ለብክነት በማይጋለጥ መልኩ መቀመጥ ይኖርበታል፤

4. ለኤጀንሲው በግዥም ሆነ በስጦታ ወይም ድጋፍ መንገድ የሚገባ ማንኛውም ንብረት ለተማሪዎችና ድጋፍ ለሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎች በሚውል መንገድ ለታለመለት ዓላማ ብቻ መዋል ይኖርበታል፤

5. ማናቸውም ለኤጀንሲው ህጋዊ ከሆኑ አካላት የሚገቡ ንብረቶች ንብረት ክፍል ገብተው የመንግስት ንብረት አስተዳደር ሥርዓትን በጠበቀ መልኩ ለሥራ አስፈላጊ በሆነ መንገድ ወጪ የሚደረጉ ይሆናል፤

6. በጥሬ ገንዘብ የሚገኝ ድጋፍ የከተማ አስተዳደሩ የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ሕግ መሰረት በማህበራዊ ትረስት ፈንድ አካውንት ገቢ መሆን ይኖርበታል፤

7. በቁሳቁስ የሚደረጉ ድጋፎች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያላለፈ፣ ንብረቱ አዲስ ወይም ያገለገሉ ስለመሆናቸው በመለየት ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት ለአገልግሎት እንዲውሉ ይደረጋል፤

8. በዓይነት የሚገኙ ሀብቶችን በየድጋፍ ዓይነቶቹ በመለየት እና ህጋዊ አሰራሩን በመከተል የዋጋ ተመን በማውጣት እንዲመዘገብ ይደረጋል፡፡

## 13. ስለክትትልና ቁጥጥር

የሚሰበሰበው ግብዓት ወይም ቁሳቁስ በሚከተለው መንገድ ክትትልና ቁጥጥር ይደረግበታል፡-

1. የተሰበሰበው ግብዓትና ንብረት በማንኛውም ሁኔታ ለብልሽት፣ለስርቆት፣ ለብክነትና ለአደጋ እንዳይጋለጥ ተደርጎ እንዲቀመጥ መደረግ አለበት፣
2. ከቁሳቁስ ውጭ ያሉ የተሰበሰቡ ሀብቶች ማለትም በጥሬ ገንዘብ እና በቼክ የተደረጉ ድጋፎች በወቅቱ በማህበረዊ ትረስት ፈንድ አካውንት ገቢ መደረጉን ክትትል ይደርጋል፣
3. የተገኘን ንብረትና ግብዓት ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ በየአመቱ ኦዲት ይደረጋል፣ እንደ አስፈላጊነቱ አስቸኳይ ኦዲት ሊደረግ ይችላል፡፡

# ክፍል አምስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 14. ስለተከለከሉ ድርጊቶች

1.ኤጀንሲው ካስቀመጠው የሀብት አሰባሰብ፣ አስተዳደርና የድጋፍ ማዕቀፍ ውጭ ተግባራትን ማከናወን የተከለከለ ነው፣

2.በዚህ መመሪያ መሠረት ከተፈቀደው እና ከሚፈቀደው አሰራር ውጭ በሆነ መንገድ በኤጀንሲው አማካኝነት የተሰበሰበውን ሀብት አስመልክቶ ተጠቃሚነትን መወሰንና ድጋፍ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

15. <u>ስለተጠያቂነት</u>

1. ማንኛውም የዚህን መመሪያ ድንጋጌ ተላልፎ የተገኘ ሰው አግባብነት ባለው ተጠያቂ ይሆናል፤
2. ከኤጀንሲ ሀብት ማሰባሰብ፣ ማስተዳደርና ማሰራጨት ጋር ተያያዥ ስራዎችን የሚሰራ ማንኛውም የአስተዳደሩ አስፈፃሚና ፈፃሚ ሠራተኛ ወይም የስራ ኃላፊ በዚህ መመሪያ የተደነገጉ ግዴታዎችንና ክልከላዎችን ተላልፎ ከተገኘ በሀገሪቱ የወንጀልና የፍትሐብሔር ሕግ መሠረት ተጠያቂ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሠራተኞች አዋጅና የዲስፕሊን መመሪያ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

16. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ እና ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

17. <u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

በኤጀንሲው ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

18. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከመጋቢት 13 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**

**መጋቢት 13 ቀን 2014 ዓ.ም**

**አንቺነሽ ተስፋዬ**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምገባ ኤጀንሲ ዳይሬክተር**